ድምፀ ተዋሕዶ

« . . . ሕዝብና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ አስተምሩ . . . » ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፱

« . . . የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ ይዳረስ ዘንድ ጸልዩልን፤ ፪ኛ . ተሰ. ፫፥፩ »

ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፪፻፱

ይህ ጋዜጣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ፣ ሥርዓት ፣ ታሪክና ጠቅላላ የግብረገብነት ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ ፣ ድምፀ ተዋሕዶ ተብሎ ተሰየመ

ያንዱ ቅጂ ዋጋ $0.10 (አሥር ሳንቲም) ፡

ቅዱስ ፓትርያርኩ አዲስ አበባ ገቡ

የዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንብረት መሆኑ አይገሠሥም ተባለ

ከ፩ሺህ ፷፻ ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ ይዞታ ሆኖ የቆየው በኢየሩሳሌም የዴር ሡልጣን ገዳም አሁንም የኢትዮጵያ ይዞታና አንጡራ ሀብት መሆኑ ተገለጸ ።

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ጉብኝታቸውን ፈጽመው አዲስ አበባ ሲገቡ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በቦሌ ኤረፖላን ማረፊያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ

ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክና የቅዱስ ሲኖዶሱ ሊቀመንበር ለ፳ቀናት በኢየሩሳሌምና በአቴንስ የሚያደርጉትን ግልጽ ጉብኝት ፈጽመው ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ- ም- አዲስ አበባ በገቡበት ወቅት ነው ።

ቅዱስነታቸው ቀደም ሲል መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ- ም- ወደኢየሩሳሌም መሔዳቸው ይታወሳል ።

ቅዱስነታቸው ወደ ኢየሩሳሌም በሔዱበት ወቅት በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ልዩ ሣሎን ለጋዜጠኞች ሰጥተውት በነበረው መግለጫ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ሀገረ

ተከታዩን በ፮ኛው ገጽ ይመልከቱ

«ጾም አትዋሉ ዘርም አትምተሩ»

ይህ ቃል የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትንሣኤ ሳምንት በቀሳውስቱ አማካይነት ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚነገር ምክር አዘል መልእክት ነው ።

ጾም መፈውስ ሥጋ መፈውስ ነፍስ እንደመሆኑ መጠን የክርስትናን እምነት የተቀበሉ ሁሉ ይጠቀሙበታል ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት ጠባቂዎችና አስጠባቂዎች ስለሆኑ ለጾም በተወሰነው ቀን ጾመው ለመብል በተፈቀደው ወቅት ደግሞ ይበላሉ ይጠጣሉ ይደሰታሉ «ካልበሉ እሬሳ» እንደሚባለው የማይበላ የማይጠጣ ሰው በሕይወተ ሥጋ ለመኖር አይችልም እግዚአብሔር በትእዛዙ እየተራመደ የሚበላውንና የሚጠጣውን ሰው አይቃወመውም እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ ላይ «ትበላለህ ትጠግባለህ እግዚአብሔርም አምላክህን ታመሰግናለህ ስለሰጠውህ ስለ መልካሚቱ ምድር » ብሎታል ዘፀ- ፰-፲ ሐዋርያው ጳውሎስም» የሚባለውም ለእግዚአብሔር ይበላል እግዚአብሔርንም ያመሰግናል» ብሏል ሮሜ ፩፤ ፲፬-፮ ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔርን የሚያስቆጣው ሕጉን ማፍረስ ነው እንጂ ለጾም የተወሰኑትን ቀናት በሚገባ ጾሞ ለመብል በተፈቀዱት ቀናት መብላትና መጠጣት መደሰትም ፈጣሪን አያስቀይምም ጠቢቡ ሰሎሞን ለሁሉም ተግባራት የተፈቀዱ ጊዜ ያቶች መኖራቸውን ሲያስረዳ ከሰማይ በታች

ተከታዩ ወደ፮ኛው ገጽ ዞሯል

ሠራተኛው ወደ ሥራው

ሥራ ወደ ሠራተኛው አይመጣም ሥራ ሊንቀሳቀስ የሚችለው በሠራተኛው ኃይል ነው ። ስለሆነም ሠራተኛ ወደ ሥራው ይሄዳል ፤ ሥራም በሠራተኛው ኃይል ከተንቀሳቀሰና ከተሠራ በኋላ ወደተፈለገበት ቦታ ሄዶ ለተፈለገው ዓላማና ጥቅም ይውላል ። በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገው ስለ ጠቅላላው ሥራ ሠራተኛ ሳይሆን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥራና ሠራተኛ ብቻ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን በሰበካ ጉባኤ እያደራጀች ራስዋን ለማስተዳደር እንድትችል ለማድረግ ጥረት በሚደረግበት በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለሥራው መቃናት እን

ተከታዩን በ፰ኛው ገጽ ይመልከቱ

በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሲካሔድ የቆየው «ትምህርተ ሱባዔ» ሰሚናር ተፈጸመ

በገነተ ጽጌ ቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሦስት ሳምንታት ሲካሄድ የቆየው ከአምስቱም አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ መንፈሳውያት ሴቶች የተካፈሉበት «ትምህርተሱባኤ» ሴሚናር መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ- ም- ተፈጽሟል ።

ሴሚናሩ በተፈጸመበት ወቅት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የትግራይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ፤ ሊቀ ሥልጣናት ገ/ማርያም ፈለቀ የቅ/ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል ።

በዚሁ ዕለት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ስብሰባውን በጸሎት እንደከፈቱ የገነተ ጽጌ ቅ/ ጊዮርጊስ የሴቶች ማኅበር ጸሐፊ ወ/ ሮ ሮማን ንግግር አድርገዋል ። ንግግራቸውን ሲጀምሩ ጥሪውን አክብረው የመጡትን እንግዶች አመስግነው በዚሁ ትምህርተ ሱባኤ ጊዜ ምን ዓይነት ትምህርት እንደተማሩና እነማን እንዳስተማሩ ፤ ከዚህም ትምህርት ምን ዓይነት ጥቅም እንዳገኙ በመተንተን ከማስረዳታቸውም ሌላ መምህራኑን በድጋሚ አመስግነዋል ።

ብፁዕ አቡነ ናትናኤል በማኅበሩ የቀረበውን የመ/ቅዱስ ሽልማት ሲሰጡ ።

ወ/ሮ ሮማን ንግግራቸውን በመቀጠል በዚህ ሴሚናር ወቅት የተሰበሰብነው መንፈ

ተከታዩን በ፭ኛው ገጽ ይመልከቱ

«ለምን ታለቅሻለሽ?

የልቅሶ ዓይነት ብዙና ሁኔታው የተለያየ ነው አባት፤እናት፤ ወንድም፤እኅት ሞቱብኝ ብሎ የሚያለቅስ አለ በተለያዩ ምክንያቶች ተመትተውና በጠቅላላ ዘመድና ወገን አጣን ብለው የሚያለቅሱም ብዙ ሰዎች መኖራቸው ግልጥ ነው ።

ማርያም መግደላዊት ያለቀሰችው ልቅሶና ያፈሰሰችው እንባ ግን ከላይ ከተጠቀሱት ለቅሶዎች ለየት ያለና የማይነጻጸር ልቅሶ ነው ። ሌሎች ሰዎች የሚያለቅሱት ዘመድ አጣን ብለው ሲሆን ማርያም መግደላዊት ያለቀሰችው ልቅሶ ግን ስለ ዘመድና ስለ ወገን ሳይሆን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራና ያለ አንዳች በደል ከበደለኞች እንደአንዱ

ተከታዩን ፪ኛው ገጽ ይመልከቱ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በየአሥራ አምስቱ ቀን እየታተመ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ
ዋና አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም
ም/ » ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር 3137
የስልክ ቁጥር 116616
አዲስ አበባ

(ርእሰ አንቀጽ)

«ፍቱትና ይሒድ!»

በዓለማችን ሦስት የሚያስደስቱ ነገሮች አሉ ፡፡ አንደኛው በጥፋቱ የታሠረ እሥረኛ የእሥራቱ ዘመን አልቆለት ነገ ልትፈታ ነው የሚል ቃል ሲሰማ ሁለተኛ ለብዙ ጊዜ ታሞ የሚማቅቅ በሽተኛ ድነህ ልትወጣ ነው የሚል ቃል ከሐኪሙ ሲነገረው ሦስተኛው ሥራ የሚፈልግ ሰው ከሥራ ውድድር ገብቶ ከተፈተነ በኋላ ፈተናውን ስላለፍክ ሥራ ልትጀምር ነው የሚል ቃል ከፈታኙ ሲሰማ በጣም ይደሰታል ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ የተስፋ ቃላት በተነገሩ ቁጥር እንደ ሙዚቃ ለሰው ጆሮ የማይሰለቹ ናቸው ፡፡

ከነዚህ በበለጠ የሚያስደስተው ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካስነሳቸው ሙታን መካከል «ፍቱትና ይሒድ» የሚለውን ቃል የተናገረው ከሞተ በኋላ ለአራት ቀን ያህል ተቀብሮ ለቆየው ለአልዓዛር ነው ፡፡ ይህም አነጋገር የቸሩ አምላካችን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ሲሆን ይህም ጥሪ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በቢታንያ መንደር አንድ ጊዜ ተሰምቶ የሚያበቃ መንፈሳዊ ጥሪ አይደለም ፡፡ ሁልጊዜ በመንፈስ የሞቱትን ሁሉ የሚቀሰቅስ ቃል ነው ፡፡

ይህም ሊሆን የቻለው እኅቶቹ የአልዓዛርን መሞት ለጌታችን ላኩበት እሱም አልዓዛር ወደ ተቀበረበት ሥፍራ መጣ ፤ ወደ አባቱም እንዲህ ሲል ጸለየ «አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ ፤ ይህንም ካለ በኋላ አልዓዛር ሆይ !! ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ ፡፡ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበር ፡፡ ኢየሱስም «ፍቱትና ይሒድ ተውት አላቸው» ኢየሱስም ያደረገውን ተአምር ካዩት ከአይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ» የዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፲፩ ቁ ፴፱—፵፭ ፡፡

ይህም ሁለት ነገሮችን ያስተምረናል ፡፡ አንደኛ ለመሥራት በምንጀምርበት ጊዜ ሥራችን የተቃና እንዲሆንና የእግዚአብሔርም መንፈስ በሰዎች ላይ አድሮ ሥራ የሚሠራ መሆኑን በዙሪያችን የሰሙት ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያምኑ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንደሚያስፈልገን ነው ፡፡ ሁለተኛ ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ሲል በተናገረው ቃል መሠረት በቢታንያ የተደረገው ተአምር እያንዳንዱ አማኝ ከመንፈሳዊ ሞት በሚነቃበት ጊዜ ሁሉ ሲፈጸምና ሳያቋርጥ የሚኖር መሆኑን እንድናውቀው ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ክርስቲያን ከኃጢአት ወደ ጽድቅ በንስሐ በሚሸጋገርበት ጊዜ ከተገነዘበት መግነዝ ሰውነቱን ሁሉ መፍታት ይገባዋል ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ እስከ ታች የተተበተበውን የመግነዝ ጨርቅ ከአልዓዛር ላይ «ፍቱትና ይሒድ» ያለው ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገረው አልዓዛር ከአሮጌ ሰውነት ተላቆ ወደ አዲስ ሕይወት እንደተሸጋገረ በዙሪያው ለተሰበሰቡት ሰዎች ለመግለጽ ነው ፡፡ አልዓዛርም ከተነሣ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላደረገው ድንቅ ሥራ መልካም ምስክር ሆኗል ብዙዎችንም ወደ እምነት ስቧል ስንክሳሩ እንደሚለው አልዓዛር በኢየሩሳሌም ጳጳስ ሆኖ ለ፴ ዓመት ቤተ ክርስቲያንን እንዳገለገለና ምዕመናንን እንዳስተማረ ይተርካል ፡፡

እንግዲህ በቢታንያ አልዓዛርን ያስነሳውና ተአምራት አድርጎ ብዙ አይሁድን ያሳመነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሆነን ሥራ የማንወደውን በስንፍና ከፈን የተገነዙትን እጆቻችንን ወደ ሥራ ዓለም እንዲሰማሩ ፍቷቸውና ይሒዱ ይለናል ፡፡ ወደ ልዩ ልዩ ክፍለ ሀገርም ሒደን ለተረሱ ሕዝቦች ያደረገውን ተአምራት ፤ የሠራውን ሥራ ስለ ጠቅላላው ዓለም መሞቱንና መነሳቱን እየዞርን ለማስተማር እንድንችል በስንፍና የተገነዘው እግራችንን ፍቱትና ይሒድ እያለ በቅዱስ ቃሉ ይጠራናል ፡፡ በተጨማሪም ስለ ክርስቶስ እንዳይመሰክር ወንጌልን ፤ እንዳይናገርና እንዳያስተምር በስንፍና መግነዝ የታሰረውን አንደበታችንን ፍቱትና ይናገር ይመስክር በማለት በቅዱስ መንፈሱ ይቀሰቅሰናል ፡፡

ይህንንም ለመሥራት በመጀመሪያ የሞተውን መንፈሳችንን በክርስቶስ ኃይል ማስነሳት ይኖርብናል ፡፡ በዚህ አኳኋን ከአሮጌው ሕይወታችን ተላቀን አዲስ ሕይወት ስለ ምንለብስ ሁሉን ለመሥራት እንድንችል ፡፡ ስለኃጢአታችን ክርስቶስ ቤዛ ሆኖ ተሰጥቶናል የኃጢአታችንንም ዕዳ ከፍሎልናል ፤ ሞትም ድል ሆኖ ተሸንፎአል ፡፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የኃጢአት ሥርየት አግኝተናል ፤ በጸጋ ላይም ጸጋ ተቀብለናል ፡፡

ስለዚህ በኃጢአት የሞቱትንና መንፈሳቸው የደነዘዙትን እንቀስቅሳቸው ከአሮጌው ሕይወታቸው እናላቃቸው አዲሱን ሰውነት ልበሱ ተብሏልና ፡፡

በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም የሰበካ ጉባኤ የሥራ ፍሬ

የሰበካ ጉባኤ መቋቋም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ሒደቱ በመጠኑም ቢሆን ጥሩ የሥራ ፍሬ አሳይቶአል ፡፡

በየጊዜው የተመረጡ አባላት ሙሉ በሙሉ የሚመሰገኑ ናቸው ባንልም ፤ ከራሳቸው ሕይወት በበለጠ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት የሚጥሩ እንዳሉ አንክድም ፡፡

ለማስታወስ ያህል በምእመናንና በካህናት ድምፅ በየጊዜው በድምፅ ብልጫ እየተመረጡ በማገልገል ላይ የሚገኙና በሥራ ውጤታቸውም ተገልጋዩንና ቤተ ክርስቲያኒቱን ያስደሰቱ የ፶ አለቃ አማረ ፈንታው ይገኛሉ ፡፡

የ፶ አለቃ አማረ ፈንታው በዚህ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መመሪያ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት የከበደውን በቤታቸው አዘጋጅተው በመምጣት ሥራው ከመቀዛቀዝ እየተጋጋለ እንዲሔድ አድርገዋል ፡፡

ይህ የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ሰበካ ጉባኤ በይበልጥ እየተጠናከረ የሔደው በእሳቸው ትጋት መሆኑን እናምናለን ፡፡ ይህ በመሆኑም ዛሬ የሰበካ ጉባኤው እርምጃ እየተጠናከረ ይገኛል ፡፡ የሰበካ ጉባኤው አባላት በዚህ ዓይነት በመሥራት የቤተ ክርስቲያኑ ክፈፍ አሠርተዋል ፡፡ የካህናቱ የወር ደመወዝ ከዓመት ወደወር ተዛውሮ አገልጋዮቹ በመደሰት ላይ ይገኛሉ ፡፡ የሰበካ ጉባኤው የጽሕፈት መሣሪያና መዛግብት ተሟልቶ በሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል ፡፡

የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ሲመሠረት ቅድሚያ እንዳለው ቢታወቅም አስታዋሽ በማጣት ወደኋላ ቀር ሆኖ ይታይ ነበር ፡፡ በዚህ በኩል ካሉት አንዳንድ ነገሮች የካህናት (መዘምራን) ልብስ ተከህኖ ጥንግ ድርብ ልብስ አሠርተው በማቅረብ ከሌሎች አድባራት እኩል ሊያስተካክሉት ችለዋል ፡፡ ይህም የሚያስመሰግን ነው ፡፡

በዕድሜ ብዛት አርጅቶ የነበረውን ዕቃ ቤት እንደገና በማደስ በጥሩ ሁኔታ በሥራ ላይ እንዲውልና ሌሎችም እድሳት የሚያስፈልጋቸውን በማሳደስ ዛሬ ቦታው አስደሳች ሆኖ ይገኛል ፡፡

በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ የቀድሞ መቃብር ቤቶችን በማሳደስ ለሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤትና ለሌላም አገልግሎት እንዲውሉ አድርገዋል ፡፡ ሌሎችንም የማይጠቅሙ መቃብር ቤቶች በውይይት እንዲነሱ አድርገዋል ፡፡ በዚሁ መነሻነት የሰበካ ጉባኤው በተለይም የ፶ አለቃ አማረ ፈንታው የሥራ ርምጃ ስላስደሰታቸው በጎ አድራጊዎች ፩ አቶ ከበደ ወ/ኪዳን ለንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ የሚሆን ቁም ሣጥን አሠርተዋል ፡፡ ፪/ በግቢው ውስጥ ውሃ ስላልገባ ብዙ ችግር ስለነበር ፶ አለቃ በሚያደርጉት ቅስቀሳ መምሬ አዘዘ ከበደ የውሃ ቧንቧ አስገብተው በውሃ በኩል ያለውን ችግር አስወግደዋል ፡፡ ሕዝቡ የሚያስቀድስበት በቅጽሩ ዙሪያ መጠለያ አሠርተዋል ፤ እያሠሩም ናቸው ፡፡



የ፶ አለቃ አማረ ፈንታው የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም የሰባካ ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር

፶ አለቃ አማረ ፈንታው የሰበካ ጉባኤውን አባላት በማንቃትና በማስተባበር ይህን ሥራውና ስንል ከግል ገንዘባቸው እያወጡ የሠሩትን ደግሞ እግዚአብሔር እንዲመዘግበው በጸሎት እናስታውሳቸዋለን ፡፡ አሁንም ይህን ዓይነቱን መንፈሳዊ ሥራ እንዳያቋርጡ በራሴና በሰበካ ጉባኤው አባላት ፤ እንዲሁም በመረጣቸው በብዙኃኑ ምእመናንና በቤተ ክርስቲያናችን ስም አደራ እላለሁ ፡፡

እንግዲህ በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ሰበካ ጉባኤ አባላትና በ፶ አለቃ አማረ ፈንታው የተካሔደው የሰበካ ጉባኤ የሥራ ፍሬ ይህ ነው ብዬ ባጭር ሳቀርብ በየጊዜው ሪፖርቱን የማስተላልፍ መሆኔን ለአንባብያን እገልጻለሁ ፡፡

የደብሩ አስተዳዳሪ
አባ ተክለ ድንግል

በጎ አድራጊው ለቤተ ክርስቲያን ድምፅ ማጉሊያ ሰጡ

አቶ ተስፋዬ ብዙ አየሁ በጐንደር ከተማ ውስጥ ለሚገኘው ለደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን (በአራት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት (፬ሺ፪፻፹፯) ብር የድምፅ ማጉያ ገዝተው የሰጡ መሆናቸውን መልአከ ገነት ዮሐንስ አምባው ገለጹ ፡፡

ለቤተ ክርስቲያን ድምፅ ማጉሊያ የለገሡት አቶ ተስፋዬ ብዙአየሁ

እኚህ በጎ አድራጊ በዚሁ ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ በአምባ ጊዮርጊስ ወረዳ ጉንትር አቦ ከተባለው ቀበሌ ከመምህር ብዙ አየሁ ትርፌ ተወልደው በፀዋትወ ዜማ በአቋቋምና በቅኔ ትምህርት ታንፀው በሃይማኖት ያደጉ ሲሆን ዛሬ በጐንደር ከተማ በንግድ ሥራ ተሠማርተው የሚሠሩና ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት የተጓደሉ ንዋየ ቅድሳትን በማሟላት ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥራዎችን የሚሠሩ መሆናቸውን መልአከ ገነት ጨምረው አስረድተዋል ፡፡

አቶ ተስፋዬ«ስጡ ይሰጣችኋል»በሚለው መንፈሳዊ መርሐ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን ፥ ለሀገሬና ለወገኔ በማለት እጃቸው ከመስጠት ወደኋላ አለማለቱን መልአከ ገነት ዮሐንስ አምባው በሰፊው ዘርዝረው አስረድተዋል ፡፡

የጋዜጣችን ዝግጅት ክፍልም አቶ ተስፋዬ ብዙአየሁ ያደረጉትንና የሚያደርጉትን መንፈሳዊ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ስም እያመሰገንን ሌሎችም ምእመናን ይህን መንፈሳዊ አላማ በመከተል የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለማቃለል ቢተባበሩ መልካም ነው እንላለን ፡፡

ከሀገር ውስጥ የተገኙ መንፈሳውያን ዜናዎች

አዘጋጅ በለጠ አበበ

በጨንቻ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሠልጠኛ ለ3 ወራት የሰለጠኑ ካህናት ተመረቁ

በጋሞ ጐፋ ሀገረ ስብከት በጨንቻ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሰልጠኛ ት/ቤት ውስጥ ከታኅሣሥ ፩ ቀን እስከ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ·ም· በሙያ ማሻሻያ የሰለጠኑ ፴፮ ካህናት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ጳጳስ ዘጋሞጐፋ በተገኙበት የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ·ም ተመርቀዋል ።

በዚሁ ዕለት ከማሰልጠኛው በወጣው መርሐ ግብር መሠረት በጨንቻ ከተማ የሚገኙ ባለሥልጣኖችና የከተማዋ ነዋሪዎች በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል

በዓሉን ከፍተኛና ደማቅ ለማድረግ በማሰልጠኛው በኮርሰኝነት ከተሰለፉ ካህናትና መምህራን ኅብረት የተዘጋጀው የመሠረተ ትምህርትን እንቅስቃሴ የሚያንጸባርቅ ትእይንት ከመታየቱ በፊት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ አጠር ባለ መግለጫና ጸሎት ከፈቱ ።

በኋላም ካህናቱ በኅብረት ታሪካዊ ዝማሬ አሰምተው የትዕይንቱ ዝግጅት በቀለጠፈ ተዋንያን ቀርቦ ሲታይ ተመልካቾችን እጅግ በጣም አስደስቶአል ። በተለይም በተሰማው መዝሙር በመደሰት ተመልካቾች በጋለ ጭብጨባ ደስታቸውን ከመግለጻቸውም በላይእያንዳንዳቸው የገንዘብ ሽልማት አድርገዋል ። በሽልማት የተገኘውንም ገንዘብ መዝሙረኛው ለአውራጃው የመሠረተ ትምህርት አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀመንበር አስረክበዋል ።

በመጨረሻም የቲያትሩ ዝግጅት እንዳበቃ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ለተመራቂዎቹ የምስክር ወረቀታቸውን በመስጠት የሥራ መመሪያቸውን ገልጸውላቸው በዓሉን በጸሎት ደምድመዋል ።

በዚሁ ዕለት ከምሽቱ ፩ ሰዓት ጀምሮ የማሰልጠኛው ት/ቤት ለተመራቂዎቹ ባደረገው የእራት ግብዣ ላይ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ፤ ጥሪ የተደረገላቸውን እንግዶችና የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባሎች ተገኝተዋል ።

በዚህም የእራት ግብዣ ላይ መምህራኑ በየተራ ለተመራቂዎቹ ምክር አዘል ትምህርት ሰጥተዋል ፤ ትምህርት የሰጡትም ፩- መ/ቤዛ ኩሉአገኘሁ የአውራጃው ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ለተከታዮቹ ያደረገውን ጥሪ አውስተው «ማንን እልካለሁ ?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ ኢሳይያስ ለጥሪው ፈቃደኛ ሆኖ እንደተነሳ ሁሉ እናንተም ለወንጌል ትምህርት በክርስቶስ ቃል መሠረት በፈቃደኛነት ተነሡ ሒዱና አስተምሩ በማለት አስተምረዋል ።

፪- ሊቀ መዘምራን ተስፋየ ደጊስ የማሰልጠኛው ሊቀመንበር ባሰሙት ንግግር በማሰልጠኛው ት/ ቤት በመስኮት ውስጥ ገብተው ማራቸውን በማበርከት ላይ በሚገኙ ንቦችመስለው ሰፋ ያለ ትምህርት ካሰሙ በኋላ ሥራችሁ ረቂቅ ፤ አንድነታችሁ የጠነከረ ፤ የሥራ ውጤታችሁ ጣፋጭና አስደሳች እንዲሆን አስፈላጊ ነው በማለት አብራርተዋል ።

፫- ዲ/ ገብረ ሕይወት ወ/ትንሣኤ ስለትምህርት ቤቱ ዕድገትእንስተው የተማሩት ካህናት ሁሉ በያሉበት ማሰልጠኛው የሚጠናከርበትን ዘዴእንዲፈጥሩ አሳስበዋል ።

፬- መ/በቃቢል መ/ጀንበሩ በየተራ ንግግር አድርገዋል ።

፭- ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባሎች አንዱ አባት

ተከታዩን ፰ኛው ገጽ ይመልከቱ

በዝዋይ ለ3 ወራት በትምህርት የሠለጠኑ ካህናት ተመረቁ

በሸዋ ሀገረ ስብከት በሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ በዝዋይ ከተማ ካህናት ማሰልጠኛ ት/ቤት ውስጥ ለ፫ኛ ጊዜ በሙያ ማሻሻያ ኮርስ የሰለጠኑ ፶፱ ካህናት መጋቢት ፳ ቀን ፸ ዓ·ም ተመርቀዋል።

በምረቃው ዕለት ብፁዕአቡነ ጐርጐርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የሸዋ ሀ/ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ካሣ ተገኝተዋል ።

ስለምረቃው በዓል በወጣው መርሐግብር መሠረት በት/ቤቱ ርእስ መምሕር መ/ገብረ ዮሐንስ አስተዋዋቂነት ንግግር ተደርጐአል።

ለተመራቂዎቹ ምስክር ወረቀት ከተሰጠ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ ባደረጉት ንግግር «ማንን እልካለሁ» ? በሚል ርእስ በመነሳት ለዚህ ጥሪ ኢሳይያስ ብቁ ሆኖ ተነስቶ እንዳስተማረ ሁሉ እናንተም የዛሬው ምሩቃን ለማስተማር መነሳት አለባችሁ ኢሳይያስ በለምጹ ምክንያትያፍር ነበር እናንተም አንዳንድ የቀሩዋችሁን ባለሟሟላታችሁ ምክንያት ነበር አሁን ግን ሁሉን ስላወቃችሁ ለማስተማር ሳታወላውሉ ተነሱ ብለዋል ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ለማስተማር ስትነሱም ስለዚህ ማሰልጠኛ እድገት ምእመናንን በማስተማር የገንዘብ አስተዋጽኦ ማድረግ አለባችሁ በማለት አሳስበዋል ።

ከዚህ ቀደም ሲል የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ባደረጉት ንግግር በዚህ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች በመንፈሳዊነት ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ ካህናትን ከኅብረተሰቡ ኩል ለማራመድ የርእዮተ ዓለም ትምህርትና የእደ ጥበባት ሙያዎችም እየተሰጡ ነው ካሉ በኋላ ዛሬ በዚህ ት/ቤት ተመርቃችሁ የምትወጡ ካህናትም ቀሰማችሁትን ተጨግራ እውቀት በተግባር መግለጽ አለባችሁ። ከዚህ በኋላ የምትሰጡት ምክንያት እንዳይኖር ተምራችሁ ተመራምራችኋልና በማለት አስገንዝበው ንግግራቸውን ለማጠቃለል ለወደፊት በዚህ ት ቤት ኮርሱ ከ፫ ወደ ፮ ወራት እንዲራዘም እየተጠና ስለሆነ ለወደፊት ችሎታችሁን በይበልጥ ለማሻሻል እንደምትችሉ ተስፋ አለኝ፣ ስለሆነም የተማራችሁትን ተግባራዊ ካላደረጋችሁት ተምሬ መጣሁ ማለቱ ግን እስወቃሽ ስለሚሆን ጠንክራችሁ ታስተምሩ ዘንድ በቤተ ክርስቲያናችን ስም አደራዬ የጠበቀ ነው ብለዋል ።

እንዲሁም የማሰልጠኛው ርእስ መምሕር መሪጌታ ገ ዮሐንስ ወ/ዮሐንስ በበኩላቸው ባሰሙት ንግግር በዚህ ማሰልጠኛ ውስጥ ለ፫ኛ ጊዜ ለመሰልጠን የተሰበሰቡት

ሀ ከሰላሌ አውራጃ
ለ/ከመናገሻ »
ሐ ከመርሐ ቤቴ »
ሐ ከመርሐ ቤቴ »
መ ከመንዝና ግሼ »

ሲሆን እነዚህም መንፈሳዊውን ትምህርት ከርእዮተዓለም ትምህርትጋር በመጣጣር መከታተላቸውን አስረድተው በእደ ጥበባትም በኩል ከልማቱ የእርሻና ቁፋሮ ትምህርት ሌላ

ሀ የብራና አወጣጥ
ለ/የቀለም አሠራር
ሐ/የቁም ጽሕፈት
መ የቃጫ ምንጣፍ
ሠ/ የግብርና መሣሪያዎች

አሠራርን በሚገባ ማጥናታቸውን ገልጸዋል ። ቀጥለውም በዚህ ማሠልጠኛ ለ፫ ወራት ሠልጥናችሁ ስትመረቁ ይህ የምስክር ወረቀት ብትሠሩበት የሚያስመሰግናችሁ ባትሠሩ በትግን የሚያስወቅሳችሁ መሆኑን በመገንዘብ ለማስተማር ቆርጣችሁ ዝመቱ፤እስከ አሁንም ባሳያችሁት ንቃትና ትጋት በራሴና በቤተ ክርስቲያናችን ስም አመሰግናለሁ» በማለት ንግግራቸውን ደምድመዋል ። ከምሩቃኑ መካከል ቄስ ሥዩም ዳኜ የተባሉት በምሩቃኑ ስም አጠር ያለ ንግግር አሰምተው ፫ ካህናት በ ተራ መወድስ ቅኔ አበርክተዋል ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የበዓሉ ፍጻሜ ሆናል ።

መምህርነት ከስብከት ጋር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ የምትፈልገው የወንበር መምህራንን ብቻ ሳይሆን አብረው ከዘመኑ ጋር የሚጓዙ የወንጌል አስተማሪዎች ያስፈልጓታል ።

ምክንያቱም የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቅድሚያ መስጠት ያለባት ለሰባኪያነ ወንጌል ከሆነ ምእመናኑ በትምህርት ስለሚማረኩ ለማንኛውም አስተዋጽኦ ለማድረግ ወደኋላ አይሉምና ነው ።

ለዚህ መነሻ የሆኑት መምህርነት ከስብከት ጋር ሲያበረክቱ የቆዩትና አሁንም በመሥራት ያሉት መምህር ዘመንፈስ ቅዱስ ሰይፉ ናቸው ።

መምህር ዘመንፈስ ቅዱስ ሰይፉ በስብከትና በቅዳሴ መምህርነት በባሌና በሲዳሞ ክፍላተ ሀገር በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ በማስተማር ያልተጠመቁትን ሲያጠምቁ የተጠመቁትን ሲያስተምሩ እንዲሁም የሙዳየ ምጽዋትንና የሰበካ ጉባኤ ጥቅም በመግለጽ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም አድርገዋል።

ከላይ ከተጠቀሰው ክፍለ ሀገር ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር ተዛውረው በወሊሶ አውራጃ ተመድበው በሚያስተምሩበት ወቅት ከጨሌና እምልኮ ባዕድ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በማድረግ ብዙዎችን ከዚህ መጥፎ ድርጊት ለመመለስ ችለዋል ።

መምህር ዘመንፈስ ቅዱስ ሰይፉ እኒህ ናቸው ።

ከዚህም ሌላ በቱሉ ቡሉ ወረዳ ከተማ ቀደም ብሎ የተሠራው የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ጠበብ ብሎ ተሠርቶ ስለነበር እኒሁ መምህር ክርስቲያኑን ሕዝብ በማስተባበር ገንዘብ እንዲያዋጡ ስለአደረጉ ሰፋ ብሎ ሊሠራ ችሎአል ።

ከዚህም ወደ ደብረ ሲና ተዛውረው በሁለት አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤን ጠቃሚነት አስረድተው የሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም አድርገዋል ።

በመርሐ ቤቴም አውራጃ ተዘዋውረው በሚሠሩበት ጊዜ በማርያምና በተክለ ሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናት ለብዙ ዘመናት የነበረውን ጭቅጭቅ አስወግደውበአንድ ሰበካ ጉባኤ እንዲተዳደር ያደረጉ መምህር ናቸው ።

ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትም ከልዩ ልዩ ድርጅቶች በማስተባበር የንዋያተ ቅድሳት ስጦታ አበርክተዋል ።

በዚሁም አውራጃ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ያልተሟላ ድርጅት ያልነበራቸውን ሕዝበ ክርስቲያኑን በማስተባበር እንዲያሟላላቸው አድርገዋል ።

አሁንም ከመሐር ቤቴ አውራጃ በኤረርና ከረዩ የሞጃ ከተማ ዙሪያ ወረዳ ሰባኬ ወንጌል በመሆን ያስተምራሉ በዚህ ወረዳም የሰበካ ጉባኤ የሚጠናከርበትን መንገድ በመቀየስ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

መምህር ለጋዜጣው ክፍል ያቀረቧቸው ብዙ የሥራ ፍሬዎች ቢኖሩም የጋዜጣ ዓምዳችን ለመቆጠብ ያህል መልካም አርአያ ይሆናሉ ያልናቸውን በዛሬው እትማችን እውተናቸዋል ።

የሆሣዕና በዓል በእንጦጦ ማርያም

ይህ በዓል መድኃኒታችን የኢሱስ ክርስቶስ ወደ ኢሩየሳሌም በአህያ ላይ ተቀምጦ በክብርና በድል አድራጊነት ሲገባ ሕፃናት አርጊቶች በአጠቃላይ ፤ የተናቁ ወገኖች የክብር ጌታ መሆኑን ተረድተው የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ሆሳዕና በአርያም ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር » እያሉ የተቀበሉትን ዕለት የሚያስታውስ ነው ።

ስለሆነም ይህ በዓል በየዓመቱ በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚከበር ቢሆንም በተለይ ጌታ በአያህ ላይ ተቀምጦ ሲገባ ምን ዓይነት አቀባበል እንደተደረገለት እንዴትም ወደኢየሩሳሌም እንደ ገባ በትርኢት መልክ በማሳየት የሚያከብሩ ሁለት ዓበይት መካናት አሉ ። እነርሱም ፩ኛዋ የእምነት መዲና የሆንችው አክሱም ስትሆን ፪ኛዋ ደግሞ መንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ናት ።

እንደተለመደው . የ፲፱፻፸፱ ዓ·ም የሆሣዕና በዓል በመንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ደማቅ በሆነ መንፈሳዊ ሥርዓት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምዕመናን በተገኙበት ተከብሯል ።

እንደአጋጣሚ የዘንድሮው የሆሣዕና በዓል የዋለው መጋቢት ፳፩ ቀን የእመቤታችን በዓል እለት በመሆኑ ለበዓሉ የምእመናን በብዛት መገኘት የተለየ ድምቀት ሰጥቶታል። በመርሐ ግብሩ መሠረት የበዓሉ አከባበርም እንደሚከተለው ነበር በአራቱ ማዕዘን ምስባክ እየተሰበከ ለዕለቱን ተስማሚ የሆነው ወንጌል በመነበብ መዘምራኑም የእለቱ ቀለም በማድረስ አሸብሽበውታል ። በዚሁ ጊዜ ጌታ ተጭኖ ወደቤተ መቅደስ የገባባት አህያ ምሳሌ የሆነችው በቅሎ አብራ በአራቱም ማዕዘን የክብር ልብስ ለብሳ ዞራለች ።



ጥንታዊቷ የእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ከዚያም ምእመናኑ በዓውደ ምሕረቱ እንደተሰበሰቡ መልአከ ፀሐይ ሣህለ ሥላሴ ወንድማገኘሁ የደብሩ አስተዳዳሪ ስለበአሉ ታሪካዊነት አጠር ያለ መንፈሳዊ ንግግር አድርገዋል ። ባሰሙት ንግግር ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ በአህያ ተጭኖ የገባው ፈረስ በቅሎ ማስጫንና ማስለጎም ተስኖት ሳይሆን የነቢያትን ትንቢታዊ ምሳሌ በመከተል ነው ትንቢቱም ነቢያት በጦርነት ጊዜ ፈረስ ጭነው ዘገር ነጥቀው የጦርነቱን መቃረብ በየአደባባዩ ይነግሩ እንደነበረ ሁሉ በሰላም ጊዜም በአህያ ተቀምጠው መነሳንስ ይዘው በአደባባዩ ይታዩ ነበር ። ምክንያቱም በአህያ የተቀመጠ አባሮ አይዝም ሮጦም አያመልጥም ለፈለገው ይገኛል ። ጌታም የሰላም ጊዜ ደርሷል የፈለገ ያገኘኛል ሲል በአህያ ተቀምጧል ብለዋል ።

የሆሣዕና በዓል በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በተከበረበት ወቅት

ከዚያም መዘምራኑ በአውደ ምሀረቱ ተሰልፈው እጅግ አስደሳች በሆነ ያሬዳዊ ዜማ «ተጽእና ዲቢ ዕዋል ኢየሩሳሌም በአህያ ቦአ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም ገባ» የሚለውን መዝሙር ለ፳ ደቂቃ. አሸብሽበዋል በዚህም ጊዜ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢየሩሳሌም ወደቤተ መቅደስ አስራ ስድስት ምእራፍ መጓዙን ለመጠየቅ አስራ ስድስት ጊዜ እየሰገዱ ወደቤተ ክርስቲያኑ በመጠጋት ከላይ በኩል ከተሰለፉት መዘምራን ጋር ተገናኝተዋል በአደባባዩ ላይ ብዙ የተለያዩ ምንጣፎች ተንጥፈዋል ። እንዲሁም መዘምራኑ እያሸበሸቡና እየሰገዱ በሚያልፉበት ስፍራ ምንጣፍ ይነጠፍላቸዋል ።

ይህም ጌታ ባለፈበት ሁሉ ልብሳቸውን ያነጠፉለት ሰዎች ምሳሌ ነው ። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኑ እድሞ በምእራብ በኩል የተለያዩ ባህርያት ያላቸው አልባሳት ተደርደረዋል ይህም የተለያዩ ወገኖች ጌታን ማመስገናቸውን የሚገልጽ ምሳሌ ነው ከዚያም እርጎው ኆኃተ መኳንንት ይባዕ ንጉሥ ስብሐት የሚለው ያሬዳዊ ዜማ ተሸብሽቧል ። በዚሁ በዓል ላይ የደብሩ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ለበዓሉ ድምቀት የሚሰጡ መዝሙሮችን በመዘመር ለበዓሉ ድምቀት ሰጥተውታል ።

ተስፋ ጥሩነህ

« ለምን ታለቅሻለሽ ? »

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ተቆጥሮ በግፍ መሰቀሉን በማሰብ ነው ።

በዚህም ምክንያት ልክናመጠን የሌለው ልቅሶ አልቅሳለች ጌታችን ኢየሱስክርስቶስበመስቀል ላይተሰቅሎ ከተቀበረ በኋላበሦስተኛው ቀን ማርያም መግደላዊት ሽቱ ልትቀባው እሑድ ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት ሲሆን እያለቀሰች ወደመቃብሩ ሄደች ይኸውም በሀገሩ ልማድ ነበር ከእስራኤል መካከል ሰው የሞተ እንደሆነ ሰውየው በሞተ በሦስተኛው ቀን ሽቱ ይቀቡት ነበርና ማርያም መግደላዊትም በዚህ ልማድ ሽቱውን ይዛ ልትቀባው ወደመቃብሩ ሄደች

ይሁን እንጂ ማርያም መግደላዊት ወደመቃብሩ ስትሄድ እንደአሰበችው ሁኖ አላገኘችውም ማለት ማርያም መግደላዊት ከቤትዋ ተነስታ ማንም ሳይቀድማት ወደ መቃብሩ ብትደርስም ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ አውቃ ትንሣኤውን ለማየት ሳይሆን ሽቱውን ቀብታ ለመመለስ ነበር ። ግን ከመቃብሩ እንደ ደረሰች መቃብሩ ተከፍቶ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶ መቃብሩን ገጥመውበት የነበረው ታላቅ ድንጋይ ተገልብጦ ስታገኘው እንግዳ ነገር ሆነባት፤ በኃዘን ላይ ኃዘን ተጨመረባት ፤ በዚህ ምክንያት ስታለቅስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበረበት መቃብር ላይ አንዱ በራስጌ ሁለተኛው በግርጌ ሁለት መላእክት ቁመው ስለነበር የኃዘንዋን ጽናት የልቅሶዋን ብዛት አይተው «አንች ሴት ለምን ታለቅሻለሽ ?» አሏት እሷም እያለቀሰች «ጌታዬን አጣሁት ወዴት እንደወሰዱትም አላውቅም እያለች ወደ ኋላዋ ዘወር ብትል ጌታን አየችው ግን ብታየውም መድኃኒታችን የኢሱስ ክርስቶስ መሆኑንአላወቀችም ነበር።

ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እጅግ ስታዝንና ስታለቅስ አይቶ እንደ ገና «ለምን ታለቅሻለሽ? »ብሏታል ።

እንዲህ ማለቱ ለጊዜው እሷን ለማጽናናትና ለማረጋገጥ ቢሆንም ፍጻሜው እኔን ሕያውን አምላክ እንዴት ከሙታን መካከል ትፈልጊኛለሽ ? እኔስ ተነስቻለሁ በማለት ትንሣኤውን እንዲያበሥሩት ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ሴቶቹ እያለቀሱ ወደመቃብሩ ደርሰው ጌታን ሲፈልጉ አይቶ ከዚያው የነበረው መልአክ እናንተ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ፤ እሱ ሳይሰቀል እነሣለሁ ብሎ ተናግሮ እንደነበር ሁሉ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል ፤ ሲል የነገራቸውን የመልአኩን ቃል ማስታወስ ይጠቅማል ።

እዎ እግዚአብሔር ለሚቀርቡት ቅርብ ሲሆን ለማይቀርቡት ግን እጅግ የራቀ ነው አንዳንድ ሰዎች በጸሎት ስንለምነው ለምን ወዲያው ጸሎታችንን ተቀብሎ ጉዳያችንን አይፈጽምልንም ? እያሉ ከዓቅማቸው በላይ ሲናገሩ ይሰማሉ ግን አባባላቸው ትክክለኛ አይደለም እያንዳንዱ ሰው በሚለምንበት (በሚጸልይበት) ጊዜ ጉዳዩ ሊፈጸምለት የማይችለው በጸሎቱ ላይ ጥርጥር ስለሚቀላቀልበት ነው ።

ግን እንደማርያም መግደላዊት ሳይጠራጠሩ በተሰበረ ልቡና እያለቀሱ ከለመኑት የማንም ሰው ልመና የማንንም ሰው ጸሎት እንደሚሰማና እንደሚቀበል በነቆርኔሌዎስ ታውቋል ።

በዚህ አንጻር ደግሞ እየተጠራጠሩ ቢለምኑት ልመናቸው ተቀባይነት እንደሌለው አያጠራጥርም ። «የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላል ያዕ ፩—፮ ተብሎ ተጽፏልና ማርያም መግደላዊትን የተመለከትን እንደሆነ ከኃጢአትዋ ብዛት የተነሣ ሰባት አጋንንት አድረውባት እንደነበርና ሰባቱንም አጋንንት ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስወጣላት በማርቆስ ወንጌል ፲፮—፱ በሉቃስም ፰—፪ ላይ ተጽፎ ይገኛል ።

ታዲያ ማርያም መግደላዊት የአጋንንት ማደሪያ ከመሆን ነጻ የወጣችው ከደዌዋም ልትድን የቻለችው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተሏና በፍጹም ልቡናዋ ሳትጠራጠር ስላመነች ው ነው ። እንግዲህ አንድ ችግር አጋጥሞን ወደ እግዚአብሔር በምንጮህበት ጊዜ ጌታችን የሚያዳምጠን ችግራችንንም የሚያስወግድልን እርሱ ብቻ ስለሆነ ሁል ጊዜ ድምጻችንን ለዘግ አድርገን ወደ. እርሱ ማስተጋባት ይኖርብናል ። ሐሳብህን ለእግዚአብሔር ግለጽለት እርሱም አሳብህን ይፈጽምልሀል ተብሎ እንደተጻፈ ያለብንን ችግር እንዲያስወግድልን ለእሱ ብቻ ሐሳባችንን መግለጽ አስፈላጊ ነው ።

እያንዳንዳችን እያለቀስን ከፈለግነው ማርያም መግደላዊትን ለምን ታለቅሻለሽ ብሎ እንዳረጋጋት የእኛንም ጩኸት ሰምቶ ዓይነ ልቡናችንን ብሩህ አድርጎ ወደ እርሱ የምንቀርብበት የሕይወትን ጐዳና ሊያሳየን ይችላል ። ከዚህም ሌላ ማርያም መግደላዊትን ያለ አንዲት ዋጋ ደርሶባት ከነበረው ደዌና አድረውባት ከነበሩት አጋንንት ነፃ እንዳወጣት እኛም በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ሁሉ ያለዋጋ የሚያክመን እውነተኛ ሐኪማችን እርሱ መሆኑን እውቀንና አምነን ከእርሱ ፈቀቅ ማለት የለብንም ።

ዳዊት ጌታዬ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና አንተ በይቅርታህ እጠበኝ እያለ ፈጣሪውን ቢለምነው ይቅርታ ሊያገኝ የቻለው ማርያም መግደላዊትም ቢሆንም የጌታታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አብሣሪ ሁና የተገኘችው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለመለየት ዋና በተሰቀለም ጊዜ በጽኑ ኃዘን ውጣበእንባዋስለታጠበች ነው እንጂ ፫ ዓመት ከ፫ ወርበኮርስ ከሠለጠኑ ደቀ መዛሙርት የበለጠ ክብር ኑሯት አልነበረም ።

በዚህ አንጻር እኛም እርሱን አምነን እያለቀስን ብንለምነው እንባችንን አብሶ ልመናችንን ተቀብሎ የፈለግነውን ሁሉ እንደሚፈጽምልንና ለማርያም መግደላዊት የተደረገላት ሁሉ እንደማይነፈገን አንጠራጠርም ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

ሠራተኛው ወደ ሥራው

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ቅፋት ሲሆኑ ይታያሉ ። የሰበካ ጉባኤ በሚገባ እንዳይዘጋጅ ልዩ ልዩ መሰናክል ያዘጋጃሉ ፤ የተመደቡበትን ሥራ በሚገባ ባለማከናወን ምዕመናንን ያሳዝናሉ ። በዚህም ምክንያት ብዙ ምዕመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣትና የሚገባቸውን አስተዋጽኦ ከማድረግ ይቆጠባሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ ያሉበት ሰበካ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁኔታ ሲያሳዝናቸው የተሻለ አገልግሎት ወደሚሰጥበት ይሄዳሉ ። ይህ ሁኔታ በተለይ ጐልቶ የሚታየው በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ነው ።

በቅርቡ በአንድ ልቅሶ ላይ የተመለከትነውን ታሪክ እንግለጽላችሁ ፤ ድርጊቱ የተፈጸመው ባለፈው ወር ነው ፤ አንድ የምናውቃቸው ሰው ሞተው ለልቅሶ እንሄዳለን ። የሟች ቤተ ሰቦች ወደአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ሄደው ፤ ቄስ ገበዙን ፈልገው ካገኙ በኋላ የሚገባውን የአገልግሎት ዋጋ እንክፈልና አስከሬኑ ወደ አለበት ቤት ሄደው ጸሎተ ፍትሐት የሚያደርሱ ካህናት ይታዘዙልን ይላሉ ፤ ቄስ ገበዙም በሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ብትከፍሉ ከቤተ ክርስቲያን ካላመጣችሁ በቀር ወደ መንደር ሄዶ ጸሎተ ፍትሐት ለማድረስ ፈቃደኛ የሚሆን ካህን አይገኝም ሲሉ መልስ ይሰጣሉ ። ነገሩ በዚህ አላበቃም ፤ የሟች ቤተሰቦች ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሄደው ፤ የዘመድ ቄስ ብናገኝ ጽንሐሕ ፤ መስቀልና ልብሰ ተክህና ይፈቀድልን አሉ ፤ አስተዳዳሪውም የተጠየቀውን ንዋየ ቅድሳት ብቻ እንዲሰጡ ለቄስ ገበዙ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ ። መሣሪያው ከተገኘ ሠራተኛ መፈለግ ግድ ሆነ ፤ እኛም በአካባቢው ተገኝተን ስለነበር ለምናውቃቸው ሁለት ቀሳውስት ችግሩን ከገለጥንላቸው በኋላ ከእነርሱ አንዱ ወደኀዘኑ ቤት እንዲሄድና በተለመደው ክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዓት መሠረት አስከሬኑን በመስቀል እየተመራ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጣ ጠየቅናቸው ፤ ቀሳውስቱ ይህን ለማድረግ ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ከነምክንያቱ ሲገልጹልን «የጠየቃችሁትን ለመፈጸም እንችል ነበር ልናደርገው የሚገባን ሥራችንም እንደሆነ እናምናለን ። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ካህናት ማንኛውም አስከሬን እኛ ወደአለንበት ካልመጣ በቀር አስከሬኑ ወደአለበት ሄደን ጸሎተ ፍትሐት አናደርስም ። ኀዘንተኞችንም አናጽናናም በማለት ወስነዋል ።» ስለዚህ ይህን ውሳኔ ተላልፈን ብንሄድ ተመልሰን የት እንገባለን?» ሲሉ አስረዱን ።

እኛም ተስፋ ሳንቆርጥ ወደ ቄስ ገበዙ ተመልሰን ከነዚህ ሁለት ካህናት አንዱ ወደኀዘኑ ቤት እንዲሄዱ ይርዱን ማለት ውሳኔውን ተላልፈህ በመሄድ መርተሃል ተብለው በካህናቱ እንዳይወቀሱ በእርስዎ ፈቃድ ይሂዱና በኋላም ከሚመጣባቸው ወቀሳ ይታደጉአቸው ስንል ጠየቅናቸው ። ቄስ ገበዙም እኔም ከእነርሱ ጋር አብሬ እንድወጣ ነውን እንዲህ የምታደርጉ ፤ በራሳቸው ፈቃድ ይሄዱ እንደሆነ እንጂ እኔስ መፍቀድ አልችልም በማለት ወደኀዘኑ ቤት ራሳቸው ለመሄድም ሆነ ሌሎች ካህናትን ለመላክ የማይችሉ መሆናቸውን አስረዱ ። በዚህ ጊዜ የተለያዩ ጥያቄዎች በመካከላችን ተፈጠሩ ፤ ጥያቄዎቹም ይህ ዓይነቱ ውሳኔ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ፤ ለወንጌል ትምህርት ፤ ለምዕመናን አንድነት ይጠቅማል ወይ ? ቤተ ክርስቲያንስ ያዘኑትን ማጽናናት ፤ የታመሙትን መጠየቅ ፤ ለሕሙማን ጸሎተ ፈውስ ፤ ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ የለባትም ወይ ? ለጸሎተ ፍትሐት ወደቤታችሁ እንመጣም ፤ የሞተባችሁም ተካፋዮች አንሆንም እናንተ ብቻ እየመጣችሁ እጅ ንሱን ፤ ስጦታንና ደጅ ጥኑን ከተባሉ ምዕመናን ቅር አይሰኙም? ምዕመናንስ ቅር ከተሰኙ ቤተ ክርስቲያን በሰበካ ጉባኤ ተጠናክራ በምዕመናን ተደግፋ ራሷን ችላ እንድትቆም የሚደረገው ጥረት ግቡን ሊመታ ይችላል ወይ ? የመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተች ጊዜ እንዴት ነበር ? ምዕመናን ራሳቸው ብቻ በራሳቸው ፈቃድ እየተሰበሰቡ መሠረቱ ? ወይስ ያላመኑትን ለማሳመን ያልተማሩትን ለማስተማር የተበተኑትን ለመሰብሰብ ከቦታ ወደ ቦታ የሚዘዋወር ነበር ወይ ? የሚሉ ናቸው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት እርሱ ራሱ ሰዎች ወደአሉበት መጥቶ ነው እንጂ ሰዎች እርሱ ወደአለበት ሂደው አይደለም ። ድውይ ሲፈውስ ፤ ሙት ሲያስነሣ የነበረውም አብዛኛውን ጊዜ ከመንደር ወደ መንደር ፤ ከከተማ ወደ ከተማ እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ነበር እንጂ እርሱ በአንድ ቦታ ተቀምጦ እነርሱ እየመጡ አልነበረም ። በኢየሩሳሌም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ ወንጌልን እየሰበከ በሕዝቡም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ነበርና አዘነላቸው ። በዚያን ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው ፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን ይልክ ዘንድ ለምኑት አላቸው » ማቴ ፱ ፤ ፴፭

በዚህ ሁኔታ እየተዘዋወረ ሲያስተምር ነበር ፤ ደቀመዛሙርቱን እንኳን አንዱን ዓሣ ሲያጠምድ ሌላውን ቀረጥ ሲቀርጥ አገኘና ለሐዋርያነት ጠራቸው እነርሱንም ከጠራቸውና ከሰበሰባቸው በኋላ «ወደዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ » ማር ፲፮ ፤ ፲፭ አላቸው እንጂ ወደ እናንተ የሚመጡላችሁን አስተምሩ አላለም ።

እንግዲህ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ፤

፩/ ሰዎች ወደአሉበት መጥቶ ፤

፪/ በየመንደሮችና በየከተማዎች በመዘዋወር ሲሆን ፤ ሐዋርያትም ከክርስቶስ በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ወንጌልን አስተምረው የተበተነውን ሰብስበው የተለያየውን አንድ አድርገው እንዴት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን መሥርተው አለፈዋል ።

ስለዚህ በክርስቶስ የተመሠረተች በሐዋርያት የተስፋፋች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን አሠረ ትምህርት ተከትላ ምዕመናን ወደአሉበት እየሄደች የታመሙትን ማጽናናት ፤ ለሞቱት ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ ይኖርባታል ፤ ይህን ባታደርግ ግን በምዕመናን መደገፍዋ አጠራጣሪ ይሆናል ። ይህንንም መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተከታዮችዋ ምዕመናን አንዱ ሲሞት አገልጋዮችዋ ካህናትን ልብሰ ተክህና አልብሳ መስቀል አሲይዛ አስከሬኑ ወደአለበት በመላክ ለሟቹ (የጉዞ ፍትሐት) ጸሎተ ፍትሐት ስታደርስ የሟች ቤተ ሰቦችንም ስታጽናና ኖራለች ። አሁን ግን በአዲስ አበባ የሚገኙ ያንዳንድ አድባራት ካህናት ወደ መንደር ሂደን ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት አናደርስም ማለት ፤ ምዕመናንን ቅር ሳያሰኝ አይቀርምና ይታሰብበት ። ከዚህም ጋር የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሥራቸው ፤

፫/ የራቁትን ማቅረብ ፤ የተበተኑትን መሰብሰብ ፤

፬/ ያዘኑትን ማጽናናት ፤ የ

ወደ ፯ኛው ገጽ ይመልከቱ

በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ...

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ላውያት ሴቶች ተመካክረን ለቤተ ክርስቲያናችን ይጠቅማሉ የምንላቸውን አስተያየትና ውሳኔዎችን ስንወያይባቸው ቆይተናል ካሉ በኋላ

ስለሁኔታውም ሲገልጡ ከመቶ በላይ ሆነን በፍቅር ስንጸልይ ፣ ጌታችን መድኃኒታችን በመካከላችን እንደነበር የታመነ ነው

ሆኖም ከዚህ ቀጥለን ይጠቅማሉ ብለን ያመንባቸውን አስተያየትና ውሳኔዎችን አሳልፈናል በማለት ውሳኔዎቹን አሰምተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ናትናኤል በበዓሉ ላይ ከተገኙት እንግዶችና በሴሚናሩ ከተካፈሉት ጋር

ው ሳ ኔ ዎ ች

፩ - ይህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የሴቶች መንፈሳዊ አንድነት ማኅበር በአምስቱ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን መግደላዊት ማርያም የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በኢየሩሳሌም ከተማ እየተዘዋወረች እንዳበሰረችና እንዳስተማረች ሁሉ እኛም የዚህን መንፈሳዊ ማኅበር አቋምና ዓላማ ለተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና መስፋፋት እንዴት እንደሚረዳ በየደብሩና ገዳማቱ እየተዘዋወርን ጠቃሚነቱን በመግለጽ ጽናበማስረዳት ለማቋቋም ተስማምተን ወስነናል ።

፪ - ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የማኅበራችን የክብር ሊቀ መንበር እንዲሆኑልን ልዩነት በሌለበት ቃል ወስነናል ።

፫ - በየገጠሩ ላሉት ችግረኞች አብያተ ክርስቲያናት ማኅበራችን ለወደፊቱ ቅዱስ ፓትርያርኩን በማስፈቀድ አጥኚ ኮሚቴዎችን መርጦ በማቋቋም አጥንተው ሲያቀርቡ በልብስና በመሳሰለው ሁሉ እንድንረዳ ተስማምተናል ።

፬ - ከቅዱስ ፓትርያርኩ በማስፈቀድ የማኅበሩ አባሎች በሙሉ በዓመት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ እየተሰበሰብን አባቶች ጳጳሳትንና ሊቃውንትን ፤ ካህናትን እየጋበዝን በሴሚናር እንድንነቃ ተስማምተን ወስነናል ።

፭ - ካህናት አባቶች መብታቸው ተጠብቆ በየጊዜው እየተሰበሰቡ ንቃተ ሕሊናቸው ከፍ እያለና እየዳበረ እኛን በመንፈሳዊ ተሐድሶ እንዲያነቁና እንዲያደራጁን ያልተቆጠበ ጥረት እንድናደርግ ተስማምተናል ።

፮ - አዕይንተ እግዚአብሔር የተባሉ ካህናት ምእመናንን መምራት ያለባቸው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ስለሆነ ፤ ይህንንም ለማድረግ በየደብሩ የሚሰጡትን ሆኖም ለአንድ ነገር ማሠሪያ አልበት እንደሚያስፈልገው ሁሉ እኛም መመሪያዎችና ትምህርቶች እየተሳተፉ ለዚህ ከፍተኛ ሐዋርያዊ ሥራ ዝግጁ እንዲሆኑንና ምዕመናንንም በተቻለ መጠን የቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑትን ካህናት የንስሐአባት እንዲያደርጉ እናሳስባለን ።

፯ - የቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች የሆኑ ወጣቶች በየመንፈሳዊማኅበራቸው ተሰብስበው መበተን ብቻ ሳይሆን ፤ በተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እንዲጠነክሩ የቤተ ክርስቲያንን ባህሏን ፤ ሥርዓቷን ፤ ታሪኳን ጠንቅቀው እንዲያውቁ በቂ የሆኑ የተዋሕዶ ሃይማኖት አስተማሪዎች እንዲመደብላቸው የየደብሩን አለቆች ሰበካ ጉባኤና እንዲሁም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ ቤትን እንጠይቃለን ።

ስለ ሴቶች መነኩሳይያት

፰ - በውጭው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሴቶች መነኮሳይያት ከፍተኛ ደረጃ ይዘው ለቤተ ክርስቲያናቸው ፤ ለሃይማኖታቸው ፤ በርካታ አስተዋፅኦ ይሰጣሉ ፤ (ያደርጋሉ) ። በኛም በተዋሕዶ እምነታችን ስለሃይማኖታችን መስፋፋትና ስለቤተ ክርስቲያናችን እድገት ለሴቶች መነኮሳይያት ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ትምህርት ብትሰጣቸው ለሃይማኖታችን መስፋፋት ፤ ለቤተ ክርስቲያችን እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚሰጡ አያጠራጥርም ።

(ይቀጥላል)

የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ ።

ሴቶች በመስቀሉ አንፃር

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለኛ ደኅንነት እንደሆነ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሲውቀውና ሲረዳውም የሚገባው ነው ።

ይሁንና እርሱ ለሰው ልጆች ደኅንነት ማለትም ወንድ ሴት ሕፃን ሽማግሌ ሳይባል በአርኣያ ሥጋ ለተፈጠረው ሰው ሁሉ ሲል ከቅድስት ማርያም ከተወለደ በኋላ ፴፫ ዓመት ከ፮ ወር በዚች ዓለም ላይ ኖሮ በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ፈተና ደርሶበታል በዚህን ጊዜ ግን ደቀ መዛሙርቱ ሲከተሉት ሴቶችም በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ለወንጌል አገልግሎት ተሳታፊዎች እንደነበር እሙን ነው ። የዚህም ፈተና መጨረሻ እንደ አንድ ክፉ አድራጊ ተቆጥሮ በመስቀል ላይ እስከ መሰቀል ደርሶአል እኛም በዛሬው ጽሑፋችን ልናተኩርበት የፈለግነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በዋለበት ጊዜ ወንዶች ደቀ መዛሙርቱ ሲበታተኑ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ያገለግሉት የነበሩት ሴቶች ግን ለኛ ደኅንነት ሲል መስቀሉን ተሸክሞ ለመሰቀል በሚጓዝበት ጊዜ ሁሉ ማንንም ሳይፈሩ እያለቀሱ ተከትለውታል በመስቀል ላይ በዋለ ጊዜም እናቱ ማርያም ብቻ ሳትሆን ብዙ ሴቶች አጠገቡ ቆመው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት የፍቅር ፣ የሰላም ፣ የአንድነትና የነፃነት ጌታ መሆኑን ተረድተው ያለቅሱ ይተክዙ እንደነበር ይነገራል።

በመስቀሉም አጠገብ ከወንዶች አንዱ ዮሐንስ ብቻ ሲሆን ከሴቶች ግን ብዙ ዙሪያውን ከበው እንደነበር ታላቁ መጽሐፋችን በዮሐንስ ወንጌል በም-፲፱-ቁ ፳፭ ላይ በደንብ ዘርዝር ያስረዳል ።

እንደዚሁም በሉቃስ ወንጌል ም-፳፫ ቁ-፵፱ ላይ ከገሊላ የተከተሉት ሴቶችም ይህን እያዩ ቆመው ነበር ይልና በቁ-፶፭ ላይ እንደገና ከገሊላም ከእርሱ ጋር ተከትለውት የመጡ ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንደሚያኖሩት አዩ ይላል ። ይህንን ጥቅስ ለመጥቀስ የፈለግነው ሴቶች ለመልካም ሥራ ማንንም የማይፈሩ ቆራጦች መሆናቸውንና ደግሞም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ሲክደው እነር ግን እንኳንስ ከመካድ ደረጃ ሊደርሱ ከአጠገቡ ሳይለዩ በመስቀሉ አጠገብ ውለው በመጨረሻም ሥጋውን ሲቀብሩ መቃብሩንም ለማየት ተከትለው መሄዳቸው ሴቶች እናቶቻችን በክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነትና ፍቅር የሚያስረዳ እውነተኛና ታማኞች መሆናቸውንም የሚያረጋግጥ ብሩህ ማስረጃ ነው ።

በትንሣኤውም ጊዜ ሴቶች አይሁድ ይገድሉናል እንሞታለን ብለው ማንንም ሳይፈሩ በሌሊት በመገስገስ ወደ መቃብሩ ሄደው መቃብሩ ክፍት ሆኖ ሲያገኙት ተጨንቀው ፤ ተጠበው እያለቀሱ ሲፈልጉት «ሂዱና መነሳቴን ተናገሩ » የሚል ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል ይህም የእነርሱን ቆራጥነት ተረድቶ በመጀመሪያ የትንሣኤውን ነገር ሴቶች እንዲያውቁና እንዲያስታውቁ አድርጓል ። እነርሱም ሳይፈሩ ሳያፍሩ የክርስቶስን ትንሣኤ በአደባባይ ደፍረው ተናግረዋል ።

ይህም የሚያመለክተው ሴቶች በተሰለፉበት ሥራ ቆራጦችና ትጉሆች መሆናቸውንና ስለ ክርስቶስ ያላቸው ፍቅር እስከ ሞት ድረስ መሆኑን ያረጋግጣል ።

ከስቅለቱና ከትንሣኤውም በኋላ ሴቶች እንዳልተለዩ ሁሉ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጸሎትና ሐዋርያትንም በመምረጥ ጊዜ ተካፋዮች ነበሩ እንደዚሁም ሴቶች የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን መሥራቾች እንደሆኑ መጽሐፍ ያብራራል።

ሴቶች ልክ እንደወንዶቹ ሐዋርያት ሁሉ ያላመኑትን በማስተማር እንዳሳመኑ ትንቢት በመናገርና በዲቁና ሥራ ሳይቀር እንዳገለገሉ እሙን ነው ።

ስለዚህ ሥራችን እነጋገራችን አስተሳሰባችን ከክርስቶስ ሥርዓት ከርሱም ፍቅር ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ቃሉ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ይላል እውነትም ያለ እርሱ ምንም ማድረግ አንችልም ስለሆነም ሰውንና እግዚአብሔርን በሚያገናኘው መንገድ መራመድና ለሌሎችም ቀናውን ጐዳና ማሳየት የሚኖርባቸው የወንዶች ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ጭምር እንደሆኑ ከላይ በቀረበው ማስረጃ ልንረዳ እንችላለን እግዚአብሔር የሚመለከተው ልባችንን እንጂ ጾታችንን አይደለም ።

አሁንም ቢሆን ራሱ ክርስቶስ ተገልጾ የተናገራቸውና ፍቅሩንም የገለጸላቸው ሴቶች በስቅለቱም ጊዜ ሆነ በትንሣኤው ጊዜ በጊዜው የነበረውን የአይሁድን ቁጣ ሳይፈሩ ወንዶች ደቀ መዛሙርቱ ሳይሄዱ እነእርሱ ገሥግሰው ሄደውከመቃብሩ አጠገብ ተዘዋውረው ይፈልጉት ለነበሩትና በትሕትና ከእርሱ ተምረው በእውነት ማስተላለፍ ለሚችሉት ሴቶች ነበር ።

ስለዚህ እኛም ወጣቶች በስቃዩ ጊዜ ከመስቀሉ ግርጌ ያልተለዩትን የቆራጥ እናቶች አርዓያ በመከተል እውነተኞችና ቆራጦች ሃይማኖታውያት ሆነን በመስቀሉ ደም የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያናችንን ለመርዳት ታጥቀን እንነሣ ።

«ጾም አትዋሉ ዘርም አትምተሩ»

ከ፭ኛው ገጽ የዞረ

ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው ለማልቀስም ለመሳቅም ጊዜ አለው» ብሏል መ/መክብብ ም-፫፤፬።

ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ ባሉት ቀናት አብር በመብላት፣ አብሮ በመጠጣት ፤ መዋዕለ ጾሙን በመንፈሳዊ አገልግሎት ጽሙዳን ሆነው የሰነበቱትን ካህናት ምሳ እየጋበዙ ማብላትና ማጠጣት ተገቢ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፵ ቀናት ጾሞ ለእኛ አርዓያነቱንና ምሳሌነቱን ስለተወልን እኛም ፵ውን ቀን ከጾምን በኋላ ከእነዚህ ቀናት ላይ ፲፭ ቀናት ጨምረን ፶፭ቀናት ጾሙን ስናበቃ ፶ ቀናት ያለ ምንም ጾም እንመገባለን ።

ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ በሚገኙት ፶ቀናት ዓብርንና ረቡዕን ሳይለዩ መደዳውን ይበላሉ? ዓርብና ረቡዕ ለምን ይበላሉ?የሚል አሳብ በአንዳንድ ሰዎች ልቡና ይጸንስ ይሆናል ሊቃውንቱ እንደዚህ ላለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ከትንሣኤ ጀምረው እስከ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ያሉት ዕለታት የሚቆጠሩት እንደ አንድ ዕለተ ሰንበት ነው በ፬ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት ሊቃውንት በኒቅያ ተሰብስበው አርዮስን አውግዘው በለዩበት ጊዜ ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ የሚገኙት ቀናትም እንደ ዕለተ ትንሣኤ እንዲከበሩ ወስነው ነበር።

ከእነርሱ ውሳኔ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ግን ሁኔታውን በማሻሻል ከ፶ው ቀናት ፰ቱ ቀናት ብቻ እንደ ዕለተ ትንሣኤ እንዲከበሩ ሲያደርጉ የቀሩት ዕለታት ሥራ እየተሠራባቸው በመብል በመጠጥ ብቻ እንዲከበሩ ወስነዋል። ይህንን መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የዳግም ትንሣኤ የፈጸምን ዕለት የበዓሉን ታላቅነት ለማስታወስ ሲሉ የመደምደሚያ ጸሎት ካደረጉ በኋላ» ጾም አትዋሉ ዘር አትምተሩ» እያሉ ምክር ለበስ መልእክት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ያስተላልፋሉ ከዚህም የተነሣ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ጦማቸውን እንዳይውሉ ዘርም እንዳይመትሩ ቤተክርስቲያናችን በየዓመቱ መልእክቷን ከማስተላለፍ አትቆጠብም ። ገበሬዎች ዘር መትረው በሰኔና በግንቦት ወራት ለመሬት የሚያበድሩት የእህል ዘርን እንዳያጡ ከአሁን ጀምረው መጠንቀቅ ይገባቸዋል ።

ለሁሉም ተግባር ልክና መልክ መጠንም ያስፈልገዋል ያለ አግባብ የሚባክን ማንኛውም ገንዘብ ሰውን ቀርቶ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም አያስደስተውም ክርስቶስ የእኛን ሥጋ እንደመዋሃዱ መጠን እንደኛ ተርቧል ተጠምቷል፤ አምላክ እንደመሆኑም መጠን ደግሞ ድውይ ፈውሷል የሞተ ሰው አሥነሥቷል ለምጻሞችን አንጽቷል ተርበው የነበሩትን ብዙ ሰዎችንም በጥቂት ኅብስት አጥግቧል ርሁባኑ በልተው ከጠገቡ በኋላ ግን የተረፈው ኅብስት ባክኖ እንዲቀር አላደረገም ። ርሁባኑ በልተው ሲጠግቡ ለደቀ መዛሙርቱ የሚሰጠው ትዕዛዝ የተረፈውን አንሡ ምንም የሚወድቅ እንዳይኖር የሚል ነበር ።

ይህም ማንኛውም ሰው ሀብቱን በከንቱ እንዳያባክን ያስተምራል አንዳንድ ሰዎች በዘመነ ፋሲካ ጠላውን አብዝተው ጠምቀው እንጀራውን በርከት አድርገው ጋግረው ዛሬ ከእኔ ቤት ነገ ከአንተ ቤት ከነገ ወዲያ ደግሞ ከእገሌ ቤት እያሉ ከመጠን በላይ አብዝተው በመብላትና በመጠጣት ውቂው ደብልቂው በማለት ዘመነ ፋሲካን አሳልፈው ለሚቀጥለው የክረምት ወራት ለችግር የተጋለጡ ሆነው ይቆያሉ ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ከችግር ላይ ከመውደቃቸው አስቀድመው መጠንቀቅ እንዳለባቸው ሊያውቁት ይገባል ።

ይህም ሲባል አብሮ መብላት ፤ አብሮ መጠጣት ተገቢ አይደለም ማለት አይደለም ፤ ከማኅበራዊ ኑሮ ዋናውና ታላቁ ቁምነገር ያለው ከሌለው ጋር ዘመድ ከዘመዱ ፤ ጐረቤት ከጐረቤቱ ጋር አብሮ መብላትና መጠጣት ነው ።

ስለዚህ ማንኛውም ሰው ዘመነ ፋሲካን ማሳለፍ ያለበት አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት ሳይሆን ፤ በመጠኑ እየበላና እየጠጣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ያደረገውን ቸርነትና የተቀበለውን መከራ በማሰብ ሊሆን ይገባል ። ከዚህም ጋር ጾምን አለመዋል ፤ ጥሪትንም አለመምተር ተገቢ ነው ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

ሠራተኛው . . .

ከ፭ኛው ገጽ የዞረ

ታመሙትን መጠየቅ ፤ ለሞቱት ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ ፪/ የወንጌል ትምህርት ለሁሉ እንዲዳረስ ብዙ ሰው ወደሚገኝበት ሁሉ መሄድና ማስተማር ሆኖ ሳለ ፤ ሥራው ወደ እኛ ይምጣ እንጂ እኛ ወደ ሥራው እንሄድም ማለት ተገቢ አይሆንም ፤ ነገሩን ለማጠቃለል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ አማኝ ሲሞት አስከሬኑ ወደሚገኝበት ቤት ሄዶ ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ ሲፈጸም የኖረና አሁንም በመፈጸም ላይ የሚገኝ የተለመደ ክርስቲያናዊ ሥርዓት ነው ።

ታዲያ ለብዙ ዘመናት ሲሠራበት የኖረውን ሥርዓት ያንድና የሁለት አድባራት አገልጋዮች ሊለውጡት ፤ ወይም ሊያስቀሩት አይችሉም ። ለአፈጻጸሙ አስቸጋሪ ሆኖ ቢገኝም እንኳን ችግሩን ለሲኖዶስ አቅርቦ ፣ ሲኖዶሱ በሚሰጠው መመሪያ ማሻሻል ይቻል ይሆናል ያለዚያ ግን ትርፉ ምዕመናንን ማሳዘንና ለቤተ ክርስቲያን የሥራ መቃናት እንቅፋት መሆን ነውና ይታሰብበት እንላለን ።

ፊዶ አስረስ

ቅዱስ ፓትርያርኩ አዲስ አበባ ገቡ

የዴር ሡልጣን ገዳም ...

ከ፩ኛው ገጽ-የዞረ

ስብከት ስለአላት የ፲፱፻፹፪ ዓ-ም የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ትንሣኤ ምክንያት በማድረግ ኢየሩሳሌም በሚገኙት መነኮሳትና ምዕመናን መካከል ተገኝተን ልባዊ የሆነ ጸሎት ለማድረግና ቡራኬ ለመስጠት ነው ብለው ነበር ።

ቅዱስነታቸው በዚሁ ዓላማ መሠረት በኢየሩሳሌም ያደረጉት ጉብኝት እጅግ የተሳካ መሆኑን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አረጋግጠዋል ።

እንዲሁም ቅዱስነታቸው ወደኢየሩሳሌም የሚሔዱት በኢየሩሳሌም በሚገኙት መነኮሳትና ምዕመናን መካከል ተገኝተው ልባዊ የሆነ ጸሎት ለማድረግና ቡራኬ ለመስጠት ስለነበረ በዚሁ መሠረት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ከቀዳም ስዑር እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ ቡራኬ በመስጠትና ቃለ ምዕዳን በማሰማታቸው ለአማንያን እጅግ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደስታ ያሳደረባቸው መሆኑ ታውቋል ።

በዚህም መሠረት መጋቢት ፳፯ ቀን ፹፪ ዓ-ም የቀዳም ስዑር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የገብረ ሰላም በዓል በከፍተኛ ድምቀት በምዕመናን መካከል ተገኝተው አክብረዋል ። በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ምዕመናንም የምሥራች የሚያበሥረውን የወይራ ዝንጣፊ ባርከው ሰጥተዋል ። እንዲሁም የትንሣኤ ዕለት ሌሊቱን ሥርዓት ጸሎቱን ሲመሩ አድረው ቀድሰው በማግሥቱ ጥዋትም ደከመኝ ሳይሉ ለምዕመናንና ለመነኮሳቱ የቁርስ ግብዣ ማድረጋቸው ታውቋል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በጠቅላላው ስለጉዞአቸውና ስለጉብኝታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ለመረዳት እንደተቻለው «በኢየሩሳሌም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ትንሣኤ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ማክበራቸውን ፤ እንዲሁም ሰኞ መጋቢት ፳፱ ቀን ፹፪ ዓ-ም የማዕዶት ዕለት ስለዴር ሡልጣን ገዳም ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው በተገኘው ውጤት የዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ሀብት መሆኑ የማይገሠሥና ማንም ሊነካው የማይችል መሆኑን ከአሥር ያላነሱ የእሥራኤል ባለሥልጣኖች ያረጋገጡ መሆኑን ቅዱስነታቸው ተናግረዋል ።

እንዲሁም በባለሥልጣኖቹና በሕዝቡ የኢትዮጵያውያን ድርሻ ለኢትዮጵያውያን የሚሆን መሆኑን ሁሉም ያመኑበት ከመሆኑም በላይ ፤ የመነኮሳቱና የገዳማችን ቤቶች በሚገባ እንዲታደሱ ከማዘጋጃ ቤቱና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው እንዲታደሱ የተወሰነ መሆኑን ገልጠዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አብረዋቸው ወደኢየሩሳሌም ሔደው የነበሩትን ፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጉጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፪ኛ/ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፫ኛ/ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በሐረርጌ የሦስት አውራጃዎች ጳጳስ ፬ኛ/ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን በቤተ ክህነት የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ፤ ፭ኛ/ሊቀ ሕሩያን መርሐ ጽድቅ ገብረ ሕይወት የፓትሪያርኩ ም/ልዩ ጸሐፊ ፤ ፮ኛ/አቶ ተስፋሁን አየለን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስከትለው ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፹፪ ዓ-ም ከጥዋቱ ፪ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ ፤ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤ አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤ ብፁዕ ጴጥሮስ በኢትዮጵያ የግሪክ ሊቀ ጳጳስ ፤ አቶ መሠረት መኰንን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ፤ የአዲስ አበባ አድባራት አስተዳዳሪዎች ፤ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ፤ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ፤ የሐዋርያዊ ድርጅት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ስለአቀባበሉ በወጣው መርሐ—ግብር መሠረት ቅዱስነታቸውን የያዘው አውሮፕላን ቦሌ እንደደረሰ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በሥፍራው በመጠባበቅ ላይ የሚገኙት እንግዶች ተቀብለዋቸዋል ። እንዲሁም አንዲት ልጃገረድ የአበባ ዕቅፍ ለቅዱስነታቸው አበርክታለች ከዚያም ቅዱስነታቸው በክብር ታጅበው መንበረ ፓትሪያርክ ቅድስት ቅዱሳን ማርያም እንደደረሱ በሥፍራው ተሰብስቦ ይጠባበቃቸው የነበረው በብዙ የም ጠር ሕዝብ በጭብጨባ እና በዕልልታ ተቀብሏቸዋል። ከዚህም ሌላ በመጋቤ ካህናት ብርሃን መኰንን የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ አማካይነት ከአዲስ አበባ አድባራት የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ መዘምራን ካህናት ተሠልፈው በዝማሬ ተቀብለዋቸዋል ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስነታቸውና እንግዶቹ ከቤተ ክርስቲያን እንደደረሱ ወደቤተ ክርስቲያን ገብተው ጉዞአቸው የተቃና እንዲሆን ለፈቀደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርሰው እንደተመለሱ በመንበረ ፓትሪያርኩ ግቢ ወደተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ እንደተገኙ በአደባባዩ ጥንግ ድርብ ለብሰው የተሰለፉ መዘምራን «ብፁዕ ወቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ ዘሐወጽኪ ለኢየሩሳሌም ምስለ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ከመ ወርኅ ንጹሕ ወከመ ኮከብ ብሩህ በጸሎትከ ትድኅን ወኢትማስን ሀገር» የሚለውን ግሥ ለ፳ ደቂቃ አሸብሽበው እንደፈጸሙ በወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የተዘጋጀው «የሰላም አባት ሰላማዊ ፤ ሰላምን አብሣሪ እንኳን ደኅና መጣህ» የሚለው መዝሙር በወጣት ልጃገረዶች እጅግ ልብን በሚመስጥ ዜማ ተዘምሮአል ።

ከዚያም በፕሮግራሙ ቅደም ተከተል መሠረት አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅ ባደረጉት አጭር ንግግር ፤ «ቅዱስነታቸው ሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌምን ጐብኝተው በሰላም በመመለሳቸው በመላው የቤተ ክህነት ሠራተኞች ስም እንኳን ደኅና መጡ እላለሁ ።

ቅዱስነትዎ ወደኢየሩሳሌም ለጉብኝት ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ በሰላም መመለስዎን ከ፲፰ ሚሊዮን በላይ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በጉጉት የሚጠብቁት ስለነበረ ፤ የቅዱስነትዎ በሰላም መመለስ የመላው ምዕመናን ታላቅ ደስታ ነው ።

የቅዱስነትዎ ጉብኝትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ኩራት ስለሆነ ፤ ሁላችንንም ደስ ብሎናል ። ሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም ዓለሙን በደሙ የዋጀው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኪደተ እግሩ ከልደቱ እስከ ዕርገቱ ተአምራት የሠራባቸውን ቦታዎችና ይህችንም ታሪካዊ ቦታ በአፌሴል የጐበኙ የመጀመሪያው ፓትሪያርክ ቅዱስነትዎ በመሆኑ ይህም የመጀመሪያው ባለታሪክ ቅዱስነትዎ ነው ።

በቅዱስነትዎ መግለጫ እንደሰማነው በዴር ሡልጣን የተገኘው ድል የቤተ ክርስቲያናችን ድል ከመሆኑም በላይ ፤ ይህን የመሰለው ታላቅ ታሪክም የቅዱስነትዎ ስለሆነ በዚህም ቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ኩራት ይሰማታል ።

ሌላው የቅዱስነትዎ ጉብኝት ያስገኘው መንፈሳዊ ድል «በጸሎተ ሃይማኖት አንድ ሆነን ሳለ በአንዳንድ የሃይማኖት የበላይነት በሚሰማቸው እኅት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ያለአግባብና በሌላቸውም መብት ፤ ዴር ሡልጣን የኛ ነው በማለት ያልሆነ ወሬ በዓለም የዜና ማሠራጫዎች በማሠራጨታቸው የቅዱስነትዎ ጉብኝት ይህንን ሁሉ ውድቅ ስለሚያደርገው ፤ ይህም ሌላው ድል ነው ብለዋል።እንዲሁም በተለይ በአሁኑ ወቅት ቤተክርስቲያን ራሷን በራሷ ችላ ለመቆም ሙከራ በምታደርግበት ጊዜ አባቶች የሠለጠኑ አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸው ታላቅ ጥቅም ያስገኛል ብለዋል ።

አቶ መርስዔ ከዚህ በማያያዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቶችዋን ባለማቅረብዋ ስለሚደርሰው ችግር ሲያስረዱ ፤ ከሁለት ዓመት በፊት የነበረው ጊዜያዊ ጉባኤ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተሰባስበው ለቤተ ክርስቲያናቸው እንዲሠሩ ሙከራ ቢደረግም እስከ አሁን ድረስ ሊሰባሰቡ አልቻሉም ። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያናችን ሥራ ሊቃና አልቻለም ካሉ በኋላ ፤ ይህንን ጉዳይ የሚመለከት ፩ድ መወድስ ቅኔ እንዲያበረክቱ ይፈቀድላቸው ዘንድ ጠይቀው የሚከተለውን መወድስ ቅኔ አበርክተዋል ።

የአቶ መርስዔ ኀዘን አበበ መወድስ ቅኔ

ኢየሩሳሌም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፤ የማን ሕሊናን ትርሣዕ እመ ረሣእናኪ ንሕነ ፤
አፍላገ ጉባኤ ባቢሎን እለ ነበርነ በከይኑ ፤
ባሕቱ ለተሐድሶ ፤ ሰቀልነ ውስተኵሐትኪዕንዚራተስፋነ፤
ብሂለነ ፈወስናሃ ፤ ለቤተ ክህነት ባቢሎን ወኢተፈወሰት በጊዜነ ።

ለዓለም

ተበሃሉሂ ሊቃውንት እለ ተዘርዑ ፍጡነ ፤
ውስተ ቤተ ክህነት ሀገረ ጥቅም መኑ ይወስደነ ፤
ወእስከ ኤዶምያስ ደብር መራሔ ፍኖት ኃጣዕነ ፤
ምጽአተ እሥራኤል ሊቃውንት እስመ ኢተሠርአ ላዕሌነ።

በማለት ያላቸውን ቅሬታ በዚህች ቅኔ ጠቁመዋል ።

በዚሁ ፕሮግራም ቅደም ተከተል የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል ።

ከነዚህም አንዱ አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ በሐዋርያዊ ድርጅት ሠራተኞች ስም ባደረጉት ሰፋ ንግግር «ከዚህ ቀደም ሲል ስለዴር ሡልጣን ገዳም ብዙ ጊዜ ድካም ተደርጎ ጉዳዩ ከፍጻሜ ሊደርስ ሲል መልእክተኞቹ የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ሳይሆኑ በሥልጣን ብቻ በመሆኑ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል ግላዊ ክብር የቤተ ክርስቲያንዋ ጉዳይ ፍጻሜ ሳያገኝ እንዲቆይ አድርገውታል። ቅዱስነትዎ ግን ጉዳዩን ለተወካዮች ባለመተውለዚህ ዓቢይ ጉዳይ ቅድሚያ በመስጠት ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ የዴር ሡልጣን ጉዳይ ፍጻሜ እንዲያገኝ ከፍተኛ ጥረት በማድረግዎ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያና ታላቅ ውለታ አድርገን ይመዘግበዋል ብለዋል ። አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ከዚህም አያይዘው ባሰሙት ንግግር ፤ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ እስከአሁን ድረስ ቅዱስነትዎ የፈጸማቸውን ዓበይት ተግባራት በመዘርዘር አስረድተው ቅዱስነታቸው በዴርሡልጣን ጉዳይ ቆራጥ ውሳኔ እንዲገኝ ጥረት እንዳደረጉ ሁሉ ፤ ወደፊትም በቤተክርስቲያን አስተዳደር አንዳንድ ቆራጥ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ የሚጠብቋቸው ብዙ አስቸኳይ ሥራዎች መኖራቸውን በሰፊው ዘርዝረው አስረድተዋል ።

ከዚያም በፕሮግራሙ መሠረት የተለያዩ ሊቃውንት በየተራ እየቀረቡ ሦስት ሦስት መወድስ ቅኔዎችን ለቅዱስነታቸው አበርክተዋል ።

ሊቃውንቱ ባቀረቡአቸው ቅኔዎች ሁሉ ቅዱስ ፓትሪያርኩ በኢየሩሳሌም ያደረጉትን ጉብኝትና የዴር ሡልጣንን ጉዳይ የሚመለከት ሆኖ ፤ ቤተ ክርስቲያንም ወደፊት አዲስ የሥራ ርምጃ እንድታደርግ የሚቀሰቅስ ነው ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስና ከመንገደኞቹ አንዱ የሆኑት ጉብኝቱ የተሳካና አስደሳች መሆኑን ገልጸው ፤ በተለይም በግሪክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልታሰበ አስደሳች አቀባበል የተደረገላቸው መሆኑን አስረድተው ፤ አቴንስ እንደደረሱ የአቴንስ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ እንግዳ መቀበያ በሆነው ገዳም እንዳስተናገዱዋቸውም አስረድተዋል ። ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በተለይ ስለ ዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ሲናገሩ «የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ጉድለቱ በግብፃውያን ብቻ ሳይሆን በእኛም የአያያዝ ጉድለት ጭምር ነው ። እኛ በሚገባ መያዝ ካለመቻላችን ጭምር ነው ። እኛ በሚገባ መያዝ ካለመቻላችን የተነሣ በጉልጉታ ከስድስት አብያተ ክርስቲያናት በላይ የተወሰዱብን መሆኑን ተናግረው ፤ አሁንም የዴር ሡልጣን ገዳማችንን እንዴት እንያዘው ? በሚለው [illegible] ተወያይተን ለወደፊቱ መደራጀት አለብን ብለዋል ። ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የውጭ አገር ሰዎች ያላቸውን አድናቆት ሲገልጹ «ቅዱስነታቸው የኖሩት በምናኔ ፤ በተባሕትዎ ሰውነታቸውን ገዝተው

ተከታዩን በ፰ኛው ገጽ ይመልከቱ

ቅዱስ ፓትርያርኩ አዲስ አበባ ገቡ . . .

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

መሆናቸው በአገር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የታወቀ ቢሆንም የውጭ አገር ሰዎች ገጻቸውንና አመጋገባቸውን አይተው ሰብአዊ ፍጡር እንደዚህ ተመግቦ ከእግዚአብሔር መንፈስ ካልተሰጠው በቀር መኖር የማይችል መሆኑን ተገንዝበው በቅዱስነታቸው መንፈሳዊ ሕይወት መደነቃቸውን ገልጸዋል።

በመጨረሻ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባሰሙት ቃለ ቡራኬ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ሆኜ ፤ ጌታ ከተወለደባት እስከ ተጠመቀባት ፤ ከተጠመቀባት እስከ ተሰቀለባትና እስከ ሞተባት ፤ እንዲሁም እስኪተነሣበትና እስከ ዓረገበት ድረስ ያደረገውን ሁሉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ጉብኝተን እጅግ ተደስተናል ።

ካህናቱ የቅዱስ ፓትርያርኩን ጉብኝት የሚመለከተውን ግራ ሲያሸበሽቡ ።

ጉብኝታችንም ለመላው የኢትዮጵያ ምዕመናን እና ለኛም ከፍተኛ ደስታ ነው ። ምክንያቱም ጉብኝታችን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ነፃነትና መብት የሚያንፀባርቅ በመሆኑ በአንዳንድ የዜና ማሠራጫዎች እንደሚወራው ሳይሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ያለምንም ተፅዕና የምንሠራ መሆናችንን ለማረጋገጥ ያስቻለን በመሆኑ የምዕመናንና የቤተ ክርስቲያናችን ደስታ ነው ብለዋል

ቅዱስነታቸው በጉብኝታቸው ከተደሰቱበት ዋናውም ምን እንደሁ ሲገልጹ ፤ በአቴንስ ያለው የካህናት ማሠልጠኛ መሆኑን ገልጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮችና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ፤ እንዲሁም በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናት ሲኖሩዋት አንድም እንኳ ቋሚ መንፈሳዊ ማሠልጠኛ ኮሌጅ ባለመኖሩ መሆኑን ገልጸው ፤ ወደፊት በተቻለ መጠን መንፈሳዊ ማሠልጠኛ ኮሌጅ እንዲኖራት ጥረት የሚደረግ መሆኑን አብሥረዋል ።

ቅዱስነታቸው በአቴንስ ስለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበል እጅግ የተደሰቱ መሆናቸውን ገልጸዋል ። በጉብኝታቸውም ወቅት ቅዱስ ጳውሎስ አምልኮተ ጣዖትን አጥፍቶ አምልኮተ እግዚአብሔርን የመሠረተባትን ቆሮንቶስንና አርዮስ ፋጎስን፤እንዲሁም በብዙመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የተለያየ መጻሕፍት የሚታተሙበትን የቤተ ክርስቲያኑዋን ታላቅ ማተሚያ ቤት በጐበኙበት ወቅት የተደሰቱ መሆናቸውን አረጋግጠዋል ።

በዚሁ ጉብኝትና አቀባበል ወቅት የአገሪቱ መንግሥት ባለሥልጣኖችም አብረው እንደ ነበሩ ተገልጿአል ።

እንግዲህ የጉብኝቱን ጠቅላላ ሪፖርት በአቀባበሉ ጊዜ የተነገሩትን ቅኔዎች ፤ እንዲሁም አቶ ሙሴ ዓለሙ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር መምሪያ ም/ኃላፊ የተናገሩትን ሙሉ ቃል በሚቀጥለው እትማችን የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን ።

ተስፋ ጥሩነህ

በኢሉባቦር 50 ካህናት የምስክር ወረቀት ተቀበሉ

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ጳጳስ ለ፫ኛ ጊዜ በጐሬ ቅድስት ማርያም ለአንድ ወር ያህል በሙያ ማሻሻያ ኮርስ ለሠለጠኑ ካህናት መጋቢት ፲፱ ቀን ፸፪ ዓ. ም. የምስክር ወረቀት የሰጡ መሆናቸው ተገለጠ ።

በዚህ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ፕሮግራም ላይ የጐሬ አውራጃ አስተዳዳሪ ጓድ ኰሎኔል ደምሴ ወርቄ ፤ ከአውራጃው ጥሪ የተደረገላቸው ባለሥልጣኖችና የሰበካ ጉባኤ አባላት ፡ የጐሬ ቅድስት ማርያምና የመቱ ቅዱስ ሚካኤል መንፈሳውያን ወጣቶች መዘምራን ተገኝተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የምስክር ወረቀት ከተቀበሉት ቀሳውስትና መምህራን ጋር፡

በወጣው መርሐ ግብር መሠረት —

፩- ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ፤

፪- ቀሲስ ብርሃኑ መንገሻ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናትና ሌሎችም በቅደም ተከተል ትምህርታዊ ንግግር ያሰሙ መሆናቸውን በደረሰን ሪፖርት ለማረጋገጥ ተችሏል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ከመቱ ቅ/ሚካኤልና ከጐሬ ቅድስት ማርያም ወጣቶች ጋር፤

በአሁኑ ወቅት በዚህ ዓይነት ለካህናት የሙያ ማሻሻያ ኮርስ መስጠት የሚያስደስት ነው ። ይህን ሥራ የሚያካሒዱ ጳጳሳትና አስተዳዳሪዎች የሚመሰገኑ ናቸው እንላለን ።

ይህም ዓይነት ኮርስ እየቀጠለ ለሁሉም የሚዳረስ ከሆነ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ፍቱን መድኃኒት እንደሚሆን እንጠራጠርም ።

በጨንቻ መድኃኔ ዓለም . . .

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ዮሐንስ ከሉቃስ ም/፲፫ የወይን አትክልተኛውን ጌታ ኢየሱስ ምን እንዳለው እናስብ ካሉ በኋላ ከዚች በለስ ፤ ፍሬ ልፈልግ ፫ ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁበትም ብሎ እንደገሰጸው ሁሉ እናንተም ፍሬ አልባ ሆናችሁ ተግሳጽእንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ ።

ይህንንም ስላችሁ ባጭሩ እንድትረዱ የምፈልገው በዚህ ማሰልጠኛ ውስጥ ለናንተ ሲባል የገንዘብና የጉልበት ኃይል ባክኗአል ፤ ስለዚህም የሰማችሁትን መንፈሳዊ ዕውቀት በንቃት በሥራ ላይ ማዋል አለባችሁ በማለት በሰፊው አስረድተዋል ።

በመጨረሻ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ «ሒዱና አስተምሩ በተኩላዎችም መካከል እልካችኋለሁ» ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት እንዳስተማረ ሁሉ እናንተም ሒዱና አስተምሩ ካሉ በኋላ እንዳያችሁት በዚህ ካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ የተለያዩ መንፈሳዊ የሥራ ፍሬዎች እየታዩ ስለሆነ እናንተም በየሔዳችሁበት የክርስቶስን መንግሥት እየሰበካችሁ በቃሉ ሕሙማንን ለመፈወስ ፤ በክርስቶስ ያላመኑትን ለማሳመንተጣጣሩ ይህንን ከማድረግ ወደ ኋላ ብትሉ ግን እስከአሁን በሊቃውንቱ እንደተነገራችሁ ወቀሳ እንዳይመጣባችሁ በትጋት አስተምሩ ብለዋል ።

ንግግራቸውን ለማጠቃለልም ስለተዘጋጀው ግብዣ የማሰልጠኛውን ሠራተኞች ፤ በትምህርት ስለደከሙት መምህራንና እስከአሁን በማስተማር ሥራ ፍጹም ተባባሪአችን የሆውን ሐዋርያዊ ድርጅትን አመስግነው ጸሎት ካደረጉ በኋላ የማታው የራት ግብዣ በዓል ተፈጽሞ ሁሉም ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ።

እኛም የምናስተላልፈው መልእክት ቢኖር በዚህ በጨንቻ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ የተማራችሁ ካህናት ሁሉ በሊቃውንቱ እንደተነገረው ሁሉ በየሔዳችሁበት በማስተማር የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የካህናትን ዕድገትና የምዕመናንን መንፈሳዊ ፍላጐት አጠናክሩ ፤ ይህ ባይፈጸም ወቀሳ ከክርስቶስ እንዳይመጣባችሁ አስቡ እንላለን ።

በለጠ አበበ

የካህናት ማኅበር ስብሰባ አደረገ

የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የካህናት ማኅበር የካቲት ፳ ቀን ፸፪ ዓ. ም. በመንበረ ፓትሪያርክ ጠ/ጽ/ቤት አዳራሽ አጠቃላይ ስብሰባ አድርጎ ነበር ። በተላከልን ሪፖርት እንደተረዳነው ስብሰባው የተደረገበት ምክንያት፡—

፩- ተደራራቢ ሥራ ስለያዙ ሰዎች ፤

፪- ስለአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች የሥራ ዝውውር

፫- ከአኅት አብያተ ክርስቲያናት ተምረው የሚመጡ ካህናት በአስተዳደር ሥራ ላይ ውለው ስለማናይ ይህ ለምን አልተደረገም ?

፬- ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት መካከል ግብረ ገብነትና ችሎታ ያላቸው ካህናት ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቢሆኑ ፤

፭- የሰበካ ጉባኤ መቋቋም ጠቅሟል ወይስ ጎድቷል ? በነዚህ ዓብይት ነጥቦች በሰፊው ከተነጋገሩባቸው በኋላ ውሳኔ አሳልፎአል ።

ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ፤

ሀ/ ተደራራቢ ሥራ ስለያዙ ሰዎች ቀደም ሲል ጉባኤው ተነጋግሮ ውሳኔውን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ማስተላለፋችን ይታወሳል ። አሁንም ለቅዱስነታቸው የምናቀርበው ለቤተ ክርስቲያናችን ጭቅጭቅን የሚያስነሣ ሆኖ ስላገኘነው ማንም ሰው ተደራራቢ ሥራ እንዳይዝ ፤

ለ/ ከውጭ አገር ተምረው የሚመጡ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ሥራ ላይ እንዲመደቡ እንዲደረግ ፤

ሐ/ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች በሥራ ዝውውር ጊዜ እንደየችሎታቸው በቤተ ክህነት በመምሪያም ሆነ በተለያዩ ሥራዎች እንዲመደቡ ፤

መ/ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ከቦታ ወደቦታ ቢቀየሩ ውጤት የለውም።ነገር ግን በትኩስ መንፈስ ሠርተው በማሠራት ለቤተ ክርስቲያንና ለአገልጋዮችዋም ውጤት የሚያስገኙ ካህናት እንዲመረጡ ፤

ሠ/ የሰበካ ጉባኤ መቋቋም ጠቃሚ ነው ። ሆኖም የሚመረጡ አባላትና ጉዳዩ በይበልጥ የሚመለከታቸው መምህረንስሐዎች ውጤትን ለማስገኘት የሚቻልበትን ዘዴ እንዲያሚሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ይህ ካልተደረገ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና ቢታሰብበት መልካም መሆኑን አስገንዝበው ውሳኔውን ለቅዱስ ፓትሪያርኩ እንዲቀርብ ወስነው በጸሎት ጉባኤው ተነሥቷል ።